የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ጥር ፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.7
ADDIS ABABA 16th January, 2023

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹/፪ሺ፲፭

የጤናውን ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት ለሚከናወነው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ..........ገጽ ፲፬ሺ፮፻

## Content

Proclamation No. 1280/2023

Italian Republic Government Loan Agreement for Financing Sustainable Development Goals Performance Fund Project Ratification Proclamation. .....................................Page 14600

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹/፪ሺ፲፭

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የጤናውን ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት ለሚከናወነው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል አስር ሚሊዮን ዩሮ (፲ ሚሊዮን ዩሮ) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሕዳር ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ ፮ኛ መደበኛ ስብሰባው ሕዳር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1280/2023

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF ITALIAN REPUBLIC

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic stipulating that the Government of the Italian Republic shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Ten Million Euro (Euro 10,000,000.00) for financing Sustainable Development Goals Performance Fund Project, was signed in Addis Ababa on 26th day of November, 2021;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its 6th regular session held on 24th day of November, 2022;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የጤናውን ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት ለሚከናወነው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሕዳር ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር F.ROT/AID 20/002/00 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን አስር ሚሊዮን ዩሮ (፲ ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Italian Republic Government Loan Agreement for Financing Sustainable Development Goals Performance Fund Project Ratification Proclamation No. 1280/2023".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement Number F.ROT/AID 20/002/00 signed in Addis Ababa on 26th day of November, 2021 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Ten Million Euro (Euro 10,000,000.00) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, on this 16th day of January, 2023.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**